# ያደረ አፋሽ

የወሬ ጦር ሜዳ ፣ እነ ፓልቶክ ሚጉ
ምላስ ባዙቃቸው ፣ ኮምፒዩተር ምሽጉ
ማይክሮፎን ቦንቡ ፣ ዝናር ፣ ስድ ማደጉ
ገሸላልጠው ጣሉት ፣ ድንቅ ነው ሲዋጉ ።

የፓልቶክ ተዋጊ ፣ ሳያውቅ ፣ ሁሉን ያውቃል
መረን ስለሆነ ፣ ገብቶ ይዘባርቃል
አላዋቂ ሳሚ ፣ ንፍጥ ይለቀልቃል
ገዳይ ተቀምጦ ፣ በሟች ይሳለቃል ።

ታጋይ ነኝ እያለ ፣ ከላይ ታች የሚለው
በተቃዋሚ ስም ፣ የተኮለኮለው
ታኝኮ ተመጥጦ ፣ ትላንት የተጣለው
የነ ፣ ስም አይጠሬ ፣ ቤትማ ፣ ቤቱ ነው
ትላንት ለወያኔ ፣ ያልሰራ ፣ እስቲ ማነው ?

ጥቅም የቀረበት ፣ አኩራፊ ተነስቶ
ትላንት የጋረደው ፣ ዛሬ ፣ የታየው ጎልቶ
መታገል ያልቻለ ፣ በአቋሙ ጸንቶ
ሙት ሲወቅስ ፣ ያመሻል ፣ ወያኔን ጎልቶ
ጽናቱን ፣ አቋሙን ፣ ገና ከሩቅ ፣ ፈርቶ ።

የተገነባውን ፣ መልሰው ሲያፈርሱ
ስር ስሩ ፣ እየሮጡ ፣ የሚልከሰከሱ
ወያኔ የጣለውን ፣ ያደረ እያፈሱ
አይገል አያቆስል ፣ ስድብ ሲተኩሱ
በወሬ ፣ ጦር ሜዳ ፣ ሲገሉ ፣ ሲያነሱ
የቀድሞ ወያኔን ፣ መልሰው ሊያነግሱ
ታጋዩን መቅበሪያ ፣ ያድራሉ ሲምሱ ።

ባደረ አፋሽ ፣ ታጋይ ፣ ችግር ላይፈታ
ትግል ሊያኮላሹ ፣ በወሬ ቱማታ
ጥይታቸው ስድብ ፣ ምላሳቸው ቃታ
ታጥቀው የዘመቱት ፣ ፈንጂው አሉባልታ
ትግልን ሳያውቁት ፣ ታጋዩ ሊረታ
በፓልቶክ ጦርነት ፣ ቀን ተሌት ፣ ድንፋታ ።

ታዛቢው ... October, 25, 2010